# ብቻ በርጩማዋን (ለበርጩማው ጌታ መወድስ)

አሣዩ

ለንግሥናህ እሾህ፣  የሆኑት ጋሬጣ፣
ማዕረግ 'ሚያሳጡህን፣ በመጥራት በሌጣ፣
የለየላቸውን፣ የምር ባላንጣ፣
በሕዝብ አሥጠልተው፣ ክብር የተጋፉትን፣
ሰጥ ለጥ ለማድረግ፣ ለመብቱ ቀናዒውን፣
አንተ እንደፈለግኸው፣ በተጠንቀቅ ቁሜ፣
እዋጋቸዋለሁ! ባሥር ጣት ፈረሜ፣
ብቻ ሥጠኝ እንጂ፣ በርጩማዋን ለኔ ።

ከቶም የማያርፉ፣ ድሮም ሥናውቃቸው፣
ሕዝቡ እንዳይገዛ፣ ለመብቱ አነሣሥተው፣
ደጉን ንጉሥና፣ ደርጉንም ተታግለው፣
አሁንም ያሉትን፣ አይፈቴ ሆነው፣
ዛሬም ይኸውና፣ ላንተም ጤና ነሥተው፣
የኛንም በርጩማ ሊጥሉት ሰባብረው፣
አይቀር መምጣታቸው፣ ዘንድሮሥ ቁርጥ ነው !!

ታድያ!

ሕዝባዊውን አመጽ፣ ኣቀጣጣዮችን፣
ሥልጣን ለሕዝብ ብለው፣ የተነሣሱትን፣
ለሥር ነቀል ሥርዓት፣ ቆርጠው የቆሙትን
አንድ ባንድ ላጠቃ፣ ካንተ ጋር ወግኜ፣
እሣት ኣቃጣዩን፣ ካመድ አዳፍኜ፣
ለሣልከው ጎራዴ፣ እጄታውን ሆኜ፣
አንተን እያወደስኩ፣ እነሱን ኮንኜ፣
ለደደቢት ቆሪጥ፣ ልካድም ታምኜ፣
ለአልሞ ተኳሾች፣ ጥይት አቀብዬ፣
ጌታዬ ደም ግብርህ፣ ምስህ ይሙላ ብዬ፣
እመርጣለሁና፣ መኖር አገልግዬ፣
ያዘዝከኝን ሁሉ፣ እፈጽመዋለሁ፣
ብቻ በርጩማዬን አደራ ብያለሁ፣
ባንተ መጀን አልኩኝ፣ ዝቅ ብዬ እሰግዳለሁ፣
ያንተ መቀመጫ፣ ወንበር እሆናለሁ።
አንተ በእኔ ላይ፣ እኔ በበርጩማ፣
ተቀምጠን ለመኖር፣ ጌታዬ እንስማማ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.